ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974


ጋዝጤጣዊ መግለጫ

ኪል- 22/07

ሰኔ 21 ቀን

# የሰላምን ማዕድ ረግጦ ስለ ሰላም መስበክ አይቻልም

ማህበራዊ ዕድገትን በሁለንተናዊ መልክ ለመጨበጥ እንድንበቃ የሰከነ እና የተረጋጋ ፍትሃዊ አስተዳደር እንደሚያስፈልግ ቅንጅት ደጋግሞ አስገንዝቧል። በዚህ የማይናወጥ መርህ ላይ አላማውን የቀየሰው ቅንጅት በሰላማዊ የምርጫ ውድድር ተሳትፎ በማድረግ ለአመፅ-አልባ የመንግስት ሥርዓት ለውጥ በፅናት መታገሉ ይታወቃል።

"...በሰላማዊ ትግል የሚያምኑ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ግማሽ መንገድ ተጉዘን እንቀበላቸዋለን..." ብሎ ሲሰብክ የቆየው ወያኔ/ኢህአዴግ በበኩሉ፣ ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያለማወላወል የቆመውን ቅንጅት አንዲት እርምጃ እንኳ አላላውስ ብሎ እነሆ እስከዛሬ ማብቂያ በሌለው አፈና በማዋከብ ላይ ይገኛል። ሰላም ለሕዝባችን ፣ ሰላም ለአገራችን ይሁን ብለው በማያሻማ ቋንቋ የቅንጅትን መርህ በአለም ዙሪያ ሳይቀር ያስተጋቡት ቅን መሪዎቹ፣ በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰው አሰቃቂ ለሆነ እስር ከተዳረጉ ሁለት ዓመታት ሊቆጠሩ ነው። የሰላምን እና የዕድገትን ራዕይ አንግበው ከቅንጅት ጎን የተሰለፉ አባላት ወይም ደጋፊዎች እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው እንደ አውሬ ሲታደኑ፣ ሲታሰሩ፣ ሲገደሉ እና አገር ጥለው ሲሰደዱ ማየት የተለመደ ነገር ሆኗል።

መሪዎቻችን፣ አባላት እና ደጋፊዎቻችን በወያኔ/ኢሕአዴግ የግፍ እስራት እንበለ-ሕግ ተንገላተዋል፣ ቤተሰብ እና የግል ንብረታቸው ተበትኖ ለመሪር ሐዘን ተዳርገዋል። ይህን እና ሕሊና ሊቀበለው የሚከብድ አያሌ በደል መቀበላቸው፣ ለሕዝብ ሰላም ሲሉ እንጂ ለግል ንብረት ወይም ክብር አለመሆኑን ማስተዋል የሚቸገር አይምሮ ያለ አይመስለንም።

እርግጥ ነው ቅንጅት ሕዝብን በሰላም አሰልፏል፣ ድምፅ በሰላም እንዲሰጥ ተግቶ ሠርቷል፣ ዓላማውን በሰላማዊ መንገድ ዳር ማድረስ የሚችልበትን ሥልት ቀይሷል ፤ ይህንንም ከሕዝብ ጋር በይፋ መክሯል። ይህ ድርጊት ወንጀል መሆኑ በአዋጅ ባይነገርም ወያኔ ግና እንደ ወንጀል ፈርጆታል። የቅንጅት መሪዎችን በማገት በኢትዮጵያ ሸንጎ ወያኔ ዛሬ ለፍርድ ያቀረበው ሰላምን እራሷን እንጂ ሌላ ማንንም አይደለም የምንለውም ለዚሁ ነው።

አቶ መለስ ዜናዊ በቅርቡ ለፓርላማ ባሰሙት ዲስኩር ስለ ሰላም ብዙ ጊዜ ወስደው ተናግረዋል። ስለ ሶማሊያ ሰላም ፣ ስለ ኤርትራ ሰላም... ወዘተ ይሁንና በንግግራቸው እጅግ አንገብጋቢ ስለሆነው የኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም አጣጥለው አቅርበዋል። የኢትዮጵያ የውስጥ ችግር ከውጥረት አልፎ ሊፈነዳ መቃረቡ እየታወቀ በቸልታና በእብሪት ለመሸፈን መሞከር፣ እርቅን መግፋት የህዝብን ቁጣ ከማባባስ ውጭ ለማንም እንደማይበጅ አበክረን እንገልጻለን።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!**

ሰላምን አጥብቀህ መሻትህ እና የቅንጅት መሪዎች ስለ ሰላም ሲባል ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ዛሬም በፅናት መቆማቸው፣ በወያኔ ዘንድ ብዙ ግምት የተሰጠው ጉዳይ አለመሆኑ ይበልጥ እየተረጋገጠ ነው። ይህ ሃላፊነት የጎደለው ድርጊት በዝምታ የሚታለፍ አይሆንም። በመሆኑም ሰላማዊ ትግላችን ውጣ ውረድ ይብዛበት እንጂ ለማይታጠፍ ድል እንደሚያበቃን በተግባር የምናስመሰክርበት ጊዜ እየተቃረበ ነው። ስለሰላም ስንል ሰላማዊ ትግላችንን ከማጧጧፍ ሌላ ምርጫ ተነፍገናል። ለፍትሃዊ የፖለቲካ ሥርዓት እውን መሆን ከቅንጅት ጎን ተሰልፈህ በቆራጥነት የታገልከው ወገናችን ለሰላማዊ ትግል ጥሪ እንድትዘጋጅ ትብብርህን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

## ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ